# ከዳውድ የተላከ ‘አሳሳቢ’ ደብዳቤ

**ታሪኩ አባዳማ ነሐሴ 2003**

አቶ ዳውድ ኢብሳ በኦሮሞ ‘ነፃነት ግንባር’ ሥም ለተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ፀሀፊ ደብዳቤ መላካቸውን ሁላችንም አውቀናል - ደብዳቤውንም አንብበነዋል። የደብዳቤው ይዘት እንደ እኔ ያሸበራቸው ብዙ ኢትዮጵያውያን የተሰማቸውን ቁጣ እና ቅሬታ በሰፊው ዕፊዋል - ጥቂት የማይባሉቱ ኦነግን ብቻ ሳይሆን ከኦነግ ጋር እየመከረ መሆኑን ሲገልፅ በቆየው ግንቦት 7 ላይ ‘ከኑግ የተገኘ ሰሊጥ’ በሚል ወርደውበታል። የግንቦት 7 እና ኦነግ በጠረጴዛ ዙርያ ተቀምጦ መነጋገር መልካም ጅምር ነው ብለው በደገፉ ግለሰቦች ላይም የ’መወያየት መልካም’ አጋንንት እንዲለቃቸው የውርጅብኝ ፀበል ተረጭቷል። ።

ከኦነግ ደብዳቤ ጥቂት ሳምንታት ቀደም ብሎ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተሰየመ አጣሪ ኮሚሽን ኤርትራ በአፍሪቃ ቀንድ በተለይም ደግሞ ኦነግን በመጠቀም አዲስ አበባ ላይ ልትሰነዝር የነበረውን ጥቃት አስመልክቶ ወደ አምስት መቶ ገፅ የሚደርስ ሰፋ ያለ ሪፖርት ቀርቧል - ያንንም ለማንበብ ዕድል አግኝተናል።[1]

ይህ የተባበሩት መንግስታት ሪፖርት ግልፅ እንዳደረገው ታቅዶ የከሸፈው ጥቃት የኤርትራን ውሱን ፍላጎት ለማራመድ ሲባል የተደረገ ‘የሽብር’ እንቅስቃሴ ሆኖ ኦነግ በመሳሪያነት መነከሩን በሰፊው አትቷል። እንደ ሪፖርቱ ከሆነ አሸባሪዋ ኤርትራ ስትሆን  ስማቸው ይፋ በሆነ የሻ’አቢያ ኮማንደሮች ትዕዛዝ ሥር የሚንቀሳቀሱ አባላቱን በማሳተፍ ኦነግ የፈፃሚነት ድርሻ ተጫውቷል።

ኤርትራን ‘ሴንጋፖር’ ለማድረግ ሻ’ኣቢያ ያለውን ፅኑ ምኞት ለማሳካት በምሥራቅ አፍሪቃ አካባቢ ነብር ሆኖ መታየት እንዳለበት ያምናል። አንዴ ነብር ከሆኑ እሰው አገር ዘው እያሉ ቡናውንም ፣ ጤፉንም ፣ ንግዱንም ያለ ተቀናቃኝ ማግበስበስ ይቻላል ብሎ ይገምታል። ይህን ስልት ለማሳካት ደግሞ በየጎረቤት አገሩ ብሶት አለኝ የሚለውን ‘ነፃ አወጭ’ ሁሉ ሰብስቦ ማሰልጠን ፣ ማስታጠቅ እና ማዝመት ነው። በምሥራቅ አፍሪቃ መረጋጋት እንዳይኖር ሻ’ኣቢያ እየሰራ መሆኑን በሰፊው የሚዘረዝረው ሪፖርት ኦብነግ እና አልሸባብን ጨምሮ እንቅስቃሴ እየተደረገ መሆኑን ይጠቁማል። ዝርዝሩን ከሪፖርቱ አንብባችሁ መረዳት ይቀላል።

የዚህ መጣጥፍ አቢይ ትኩረት - ኦነግ ለተመድ ዋና ፀሀፊ ዛሬ ይህን አይነት ደብዳቤ መፃፍ ለምን ፈለገ? ብሎስ ደብዳቤው ያዘለው አዲስ ነገር አለ? ከሆነስ ምን መደረግ አለበት የሚሉትን ነጥቦች በአጭሩ ለመዳሰስ ነው።

ወደ ተነሳሁበት ከመግባቴ በፊት ግን ከጉዳዩ ጋር ተወራራሽነት አላቸው ብዬ ያመንኩባቸውን ጥቂት አስረጂዎች ለአንባቢ ግንዛቤ እንዲረዳ ላቅርብ። የኤርትራን አሸባሪ እርምጃ ተከታታይነት ይፋ ያደረገው የተመድ  ሪፖርት በወጣ ማግስት ኤርትራ ላይ ተጨማሪ ማዕቀብ ሊወሰድ ይችላል የሚል ወሬ በዲፕሎማሲ ኮሪዶሮች እየተናፈሰ ነው። ይህ ያሳሰበው ሻ’አቢያ ጉዳዩን ለማርገብ ሲል ይመስላል ተከታታይ ዲፕሎማሲያዊ ፣ ስልታዊ እና የፕሮፓጋንዳ እርምጃዎች በመውሰድ ላይ ይገኛል - ከብዙ በጥቂቱ፦

- ረግጦ የወጣውን የምሥራቅ አፍሪቃ የንግድ ቀጠና IGAD መልሶ ለመቀላቀል ጥያቄ አቅርቧል
- የ ሻ’አቢያው መሪ ያልተጠበቀ ጉብኝት በዩጋንዳ አድርጎ በዚያ ለሰላም የቆመ መሆኑን ሰብኳል
- አልሸባብ ሞቃድሾን ለቆ እንዲያፈገፍግ ተደርጓል
- ኦነግ ፣ ኦብነግ እና አልሸባብ እና የጂቡቲው አማፂ ቡድን ለተመድ ደብዳቤ እንዲፅፉ ሆኗል

እነኝህ እርምጃዎች በሁለት ሳምንት ግዜ ውስጥ በተከታታይ የተወሰዱ ሲሆኑ - እርምጃዎቹ ከጥቂት ወራት በፊት ይሆናሉ ተብለው የሚታሰቡ አልነበሩም።

እንግዲህ አቶ ዳውድ ኢብሳ በዚህ በአሁኑ ግዜ ለተባበሩት መንግስታት ደብዳቤ ለመፃፍ የተነሱት የተመድን ፀሀፊ ትኩረት የሚጠይቅ ከድርጅታቸው የትግል አጀንዳ ጋር የሚዛመድ ልዩ ወይም እንግዳ ነገር ስለተከሰተ ሳይሆን ከ ሻ’አቢያ ጋር በፈጠሩት ሚዛናዊ ያልሆነ ሽርክና የተከተለውን መዘዝ ለማድበስበስ የድርሻቸውን ለመወጣት ሲሉ ነው። ሸ’ኣቢያ ፍላጎቱን ለማራመድ ሲል የሚጠቀምባቸው የጎረቤት አገር ‘ነፃ አውጪ’ ድርጅቶች እንደ አስፈላጊነቱ ቦምብ ለማፈንዳት እንደሚላኩ ሁሉ አንወክለዋለን በሚሉት ህዝብ ስም ደብዳቤ በማርቀቅ

---

[1] **Case study: planned “Oromo Liberation Front” operation to disrupt the African Union summit**

የሻ'ኣቢያን ዲፕሎማሲያዊ ትግል ያግዛሉ። አቶ ዳውድ ኢብሳ አቢይ ትኩረታቸው የህዝብ መብት እና የጋራ ብልፅግና ሳይሆን የሻ'ኣቢያ ህልውና እና በውጭው ዓለም የሚኖረው ነው።

በመሆኑም ደብዳቤው ስለ ኦነግ የትግል አላማ የሚናገር ይምሰል እንጂ አቢይ ትኩረቱ በፀረ-ኢትዮጵያዊነቱ እና አሸባሪነት ስሙ የለየለትን ሻ'አቢያ 'የነፃነት ተዋጊዎች አለኝታ' አድርጎ ለመሳል የታለመ ነው። እና የሻ'አቢያን ገፅታ ለማሳመር ሲሉ ድፍን ኢትዮጵያዊ ወገናቸውን ያሳዘነ መርዘኛ መልዕክት ማርቀቅ መርጠዋል።

በአሁኑ ወቅት ኤርትራ አሰልጥና እና አስታጥቃ በወያኔ ላይ የምታዘምተው ማናቸውም ወታደራዊ ሀይል ከራሱ አላማ ይልቅ የኤርትራን ፍላጎት የሚያረጋግጥ ተግባር ለመፈፀም እንደሚገደድ ከሻ'አቢያ ተፈጥሮ በመነሳት መናገር ይቻላል - የተመድ ሪፖርት ይህንኑ የኤርትራ ባህሪ በሪፖርቱ አንፀባርቋል።

የመንግስታቱ ድርጅት ሪፖርት 'ኤርትራ ሽብር ልትነዛ ነበር...' - ይልና ሲቀጥል 'የኦነግን አባላት ለጥቃቱ አሰልጥና አዘምታለች...' ሲል ያብራራል። የኦነግ ሚና የኤርትራን ወይንም የሻ'አቢያን እኩይ ፍላጎት ማርካት መሆኑን ሪፖርቱ ደጋግሞ አብራርቷል። ኦነግ በራሱ መርህ ላይ ተመርኩዞ የሚያደርገው እንቅስቃሴ እንደሌለ የሚያመለክት ጉዳይ በመሆኑ በውነቱ ለኦነግ አሳፋሪም አሳዛኝም ነው። የኦነግ አባላት እና ደጋፊዎቹም ቢሆኑ ይህን በገለልተኛ አካል የቀረበ ታማኒነት የጨበጠ ሪፖርት ሲያዩ - ድርጅታቸው ቆሜለታለሁ የሚለውን አቢይ ጉዳይ ትቶ ጨርሶ በማይመለከተው የወያኔ እና ሻ'አቢያ ቅራኔ መጠመዱ ደስ የሚላቸው አይመስለኝም። ምናልባትም የዳውድን አመራር ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ብርቱ ጉዳይ ነው የሚል ስጋት አለኝ።

የተመድ ሪፖርት እንዳመለከተው የኦነግ ተልዕኮ ካንድ ዙር ፈንጂ ጥቃት የዘለለ አይደለም። ከዚያ ፍንዳታ በሁዋላ ምን እንደሚደረግ በርግጠኝነት የሚያውቀው ሻ'አቢያ ብቻ ሲሆን - ኦነግ በበኩሉ በተጠንቀቅ ቆሞ ትዕዛዝ ይጠብቃል ማለት ነው። ምክንያቱም ፈንጂዎች ሳየቀሩ የሚጓጓዙት ከኤርትራ በመሆኑ ሁሉም ነገር በሻ'አቢያ ፈቃድ እና እቅድ ውስጥ ሆኖ እንደ አመቺነቱ የሚቀጥለው ተግባር በአስመራ ይወሰናል።

እንደ ሪፖርቱ አቀራረብ ከሆነ ሻ'አቢያ በኦነግ በኩል ሰላማዊ ኢትዮጵያውያን በሚኖሩበት አካባቢ የእልቂት ፈንጂ ለማፈንዳት ዝግጅቱን አጠናቆ ነበር። እንግዲህ በማናቸውም መለኪያ ይሄ በጎ ስም የሚያስገኝ ድርጊት አይደለም። በተመድ አጣሪ ሪፖርት ውስጥ የኦነግ ስም በተላላኪነት ተደጋግሞ መነሳቱ የአቶ ዳውድ ድርጅት በአለም አቀፉ ህብረተሰብ ዘንድ መጥፎ ስም መያዙን ያመለክታል። 'ጥቁር ነጥብ' ውስጥ ገብቷል።

የኦሮሞ ህዝብ መብት የሚረጋገጠው አንድ ሰሞን ወይንም ባንድ የመሪዎች ስብሰባ ወቅት አዲስ አበባን በፈንጂ በማተራመስ ነው ብሎ የሚያምነው ሻ'አቢያ ብቻ ነው። ምክንያቱም ያንድ ሰሞን የፈንጂ ትርምስ ሻ'አቢያ በሚፈልገው መልኩ ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላም እንደሌለ ያመለክት እንደሆን እንጂ ጥቃቱ የመብት ጥያቄ ትግል ነው የሚል ግምት ያሳድራል ብሎ ማሰብ ብልህነት የጎደለው ስሌት ነው። ሻ'አቢያ ይህን ጠንቅቆ ያውቃል - አቶ ዳውድ ግን የተገለፀላቸው አይመስልም። በደብዳቤያቸው እንዳመለከቱት - ሪፖርቱ እንዳስቀመጠው ሳይሆን ኦነግ "የሚታገለው ከኢትዮጵያ ቅኝ አገዛዝ ነፃ ለመውጣት..." ነው።

በኔ እምነት አቶ ዳውድ ለተመድ ድብዳቤ ለመፃፍ የተነሳሱበት ሌላው ምክንያት በተመድ ሪፖርት ውስጥ የተንፀባረቀውን 'ኦነግ የኤርትራን መንግስት ተልዕኮ እየፈፀመ ነው' የሚለውን የወረደ የሥራ ድርሻ ለማስተባበል ነው። 'ከቅኝ ግዛት ነፃ ለመውጣት ትግል እያካሄድን ነው' በማለት ኦነግ ፍልሚያ ላይ መሆኑን በመጠቆም የተመድ ሪፖርት ስለ ኦነግ ያሳደረው ግንዛቤ የተሳሳተ መሆኑን ለማሳየት የተፈለገ ይመስላል። እንደ አሸባሪ ሳይሆን እንደ ነፃ አውጭ ተቀበሉን የሚል ጥያቄ ያዘለ ደብዳቤ ነው።

በውነቱ የአቶ ዳውድ አላማ የድርጅታቸውን 'ፍትሀዊ' ትግል ለማሳየት ከሆነ ደብዳቤውን ለማርቀቅ ለምን ይህን ግዜ መረጡ? ሻ'አቢያ ዛሬ ከዓለም ህብረተሰብ መነጠሉ እየተባባሰ የመጣበት መሆኑን የማይገነዘብ አለ ብለው ይገምቱ ይሆን? ኦነግ በሚያቀርበው ይህን የመሰለ ውል የሌለው ደብዳቤስ የሻ'አቢያን እኩይ ተፈጥሮ መቀባባት እና ሌላ መልክ እንዲኖረው ማድረግ ወይም ማገዝ ይቻላል?

የአቶ ዳውድን ደብዳቤ በሌላ ጎኑ ስናየው ደግሞ በሪፖርቱ ውስጥ የቀረበውን ጭብጥ ዋጋ ለማቃለል ሲሉ 'ከሽፈ የተባለውን ጥቃት ብንፈፅም እንኳ ብሶት እና ጥያቄ ስላለን ነው' በሚል የትግላቸውንም ሆነ የሻ'አቢያን ድጋፍ ፍትሀዊነት ለማሳየት የፈለጉ ይመስላል። በዚህም ዳውድ ተገንጣይ እንጂ "አሸባሪ አይደለንም" - ለማለት ነው የሞከሩት። እናም ኤርትራ የምትረዳው ለነፃነት ተዋጊ እንጂ ለአሸባሪ አይደለም የሚል ግንዛቤ

ለመፈንጠቅ። የመገንጠል ጥያቄ ሲቪል ታርጌቶችን በማጥቃት ጭምር ቢካሄድ አያስከስስም ፣ አያስጠይቅም የሚሉም ይመስላል - ማን እንደተጠየቀ?

ይሁንና ደብዳቤው የታለመለትን ግብ መቷል ማለት ያስቸግራል።

በአፍሪካ ታሪክ የመጨረሻዋ ቅኝ ግዛት ናሚቢያ ነች ብሎ ለደመደመው የተመድ ይሄ አዲስ ነገር ነው። ልክ ፈንጣጣ ከምድረ ገፅ ጠፍቷል ብሎ ባወጀ አሥር ዓመቱ ሌላ ፈንጣጣ በሆነ የዓለም ክፍል ተቀስቅሷል እንደማለት ያህል። ደብዳቤው ኦነግ እውነትም የሚያደርገውን የማያውቅ ፣ በራሱ የማይመራ መሆኑን ያመለክታል።

እዚህ ላይ ቅኝ ግዛት ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ ለማብራራት አልቃጣም - ግዜ ማባከን መስሎ ይታየኛል።

ይሁንና እንደ ኩሩ ኢትዮጵያዊነቴ እና እንደ ኦሮሞ ተወላጅነቴ በአገሬ ውስጥ ቅኝ የተገዛሁ መሆኔን ከቶ አልቀበለውም። የመናገር እና የመፃፍ መብቴ ተረግጧል? እንዴታ! በነፃ የመደራጀት እና የፈለኩትን የፖለቲካ መስመር መደገፍ መብቴ ተረግጧል? እንዴታ? በቅኝ ግዛት ሥር እየተገዛሁ ነው? እእእ

እንደ እውነቱ ከሆነ ኦነግ ለሚያራምደው የመገንጠል አላማ ከተሰዉት ኦሮሞዎች ይልቅ ለኢትዮጵያ ሉአላዊነት መረጋገጥ ፣ ለዳር ድንበሯ መከበር ሲሉ ህይወታቸውን የገበሩ ኦሮሞዎች ቁጥር በብዙ መቶ ሽህዎች ይበልጣል። የዛሬይቱን ኢትዮጵያ እውን ለማድረግ ሲሉ በሁሉም የሙያ ዘርፍ - በዓለም የኦሎምፒክ አደባባይ ጨምሮ ባንዲራችንን ከፍ አድርገው ያውለበለቡ የኦሮሞ ተወላጅ የሆኑ ኩሩ ኢትዮጵያውያን ሺህ በሺ ናቸው።

ዳር ድንበር እና ሉአላዊነት እንዲህ እንደ አሁኑ ተለይቶ ተለክቶ ድንጋይ ተተክሎ ካርታ ተስሎ ባልታወቀበት ዘመን ለግጦሽ መሬት እና ውሀ ፍለጋ ጥንት የተካሄደውን የጎሳዎች ግጭት እና የመስፋፋት ውድድር እንደ ቅኝ አገዛዝ ወረራ አድርጎ ለጠባብ እና አፍራሽ አላማ መተርጎም ዛሬ ጠቃሚ አይመስለኝ።

ኦነግ በኦሮሞ ህዝብ ስም የተደራጀ የፖለቲካ ሀይል ነው። የዶር መረራ ጉዲና ፣ የአቶ ቡልቻ ደመቅሳ ድርጅቶችም እንዲሁ በኦሮሞ ህዝብ ስም የተደራጁ ናቸው። አቶ ዳውድ ከዶር መረራ እና ከቡልቻ ደመቅሳ የተሻልኩ ኦሮሞ ነኝ ካለሉን በስተቀር እሳቸው ብቻ ናቸው ቅኝ ግዛት የሚል ያፈጀ ፈሊጥ የያዙት።

ዶር መረራ ፣ አቶ ቡልቻ ... እንደ እኔ ያለ ተራ ኢትዮጵያዊ ጨምሮ ወደ ሀያ ሚሊየን የሚጠጋው የኦሮሞ ህዝብ ችግር ከሌላው ኢትዮጵያዊ ችግር ተነጥሎ የማይታይ ፣ ብሎም መፍትሔውም አገሪቱ ውስጥ በህግ የበላይነት የተረጋገጠ እኩልነት ሲኖር ብቻ ነው ብሎ ያምናል። ለዚህም ቀላሉ መንገድ ኤርትራ ተሻግሮ ፈንጂ እና ጥይት መለመን ሳይሆን ከሌሎች ዲሞክራሲያዊ ዝንባሌ ካላቸው ኢትዮጵያውያን ጋር ተቀራርቦ ግልፅ ውይይት በማድረግ እና ለሁሉም የሚበጅ ስልት በመቀየስ ብቻ ነው።

በአገራችን ተንሰራፍቶ የቆየውን አምባገነናዊ የመንግስት አስተዳደር መለወጥ እና ሁሉም ዜጋ በባለቤትነት ስሜት ሰብአዊ መብቱ በህግ የበላይነት ፀድቆ እንዲኖር መታገል ተገቢ እና ፍትሀዊም ነው። አቶ ዳውድ ስለ ቅኝ አገዛዝ ከሚሰብኩን ይልቅ ስለ አንድነታችን ቢቆረቆሩ ፣ በጋራ መገንባት ስለሚገባን ሁዋላ ቀር አገራችን ጉዳይ ቢከነክናቸው ፣ ኢትዮጵያን በደማቸው እና አጥንታቸው የጠበቋት ሁሉም ዜጎች ሰብአዊ መብታችን ስለሚረጋገጥበት የፖለቲካ ሥርዓት ግድ ቢላቸው ትግሉም ሆነ ስልቱ ትርጉም ያለው ይሆናል። ወያኔ በህዝብ ላይ የጫነውን ከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ ሰብሮ ብሎም በዘር አድልዎ ላይ ተመስርቶ ለጥቂት ታማኞቹ ጥገት ያደረጋትን አገር ነፃ ማውጣት ትርጉም ያለው ታሪካዊ ተግባር ነው። ይህ ሲሆን ጉዳዩን ለሚያየውም ሆነ ለሚሰማው የውጭ ታዛቢ እውነትነት ያለው ጭብጥ ማቅረብ ይቻላል።

በሻ'ኣቢያ ትዕዛዝ ለሻ'ኣቢያ ፍጆታ የሚሆን ደብዳቤ በኦሮሞ ህዝብ ስም ለተመድ መፃፍ የኦሮሞን ህዝብ ክብር መድፈርም ማዋረድም ነው።

በመጨረሻም - ግንቦት 7 ከኦነግ ጋር ለምን ይወያያል ብለው ለሚወራጩት ወገኖች የምለው አንድ ነገር ቢኖር - ቀደም ባሉት ዓመታት የኤርትራን ችግር ለመፍታት በወታደራዊ ሀይል ብቻ ተጠቀመ የሚል በደርግ ላይ የከረረ ክስ ሲቀርብ እንደነበር የምናስታውሰው ነው። ዛሬ ድረስ ደርግ ከሚከሰስባቸው ነጥቦች አንዱና ዋንኛው ነው። 'የምታገለው ለኤርትራ ነፃነት ነው' ብሎ በግትርነት ከቆመው ከሻ'አቢያ ጋር ደርግ መነጋገር መደራደር ነበረበት የሚል ፅኑ አቋም አላቸው። ታዲያ ወታደራዊ ብቻ ሳይሆን ድርድር አስፈላጊ መሆኑን ያን ግዜ ያምኑ የነበሩ

*ፖለቲከኞች ዛሬ ያውም ምንም አይነት ፖለቲካዊ ሥልጣን የሌለው ኢትዮጵያዊ ድርጅት ልገንጠል ከሚለው ኦነግ ጋር ተቀራርቦ ቢነጋገር ለምን እንደ ጥፋት ታያቸው? እነሱ ስልጣን ላይ ቢወጡ የኦነግን ጥያቄ እንዴት ያስተናግዳሉ? በጠመንጃ ወይንስ በውይይት? ወይንስ እነሱ ስልጣን ላይ ሲወጡ ኦነግ የሚባል ድርጅት ህልውናው አብሮ ይከስማል?*

*በመሠረቱ የአገራችን ፖለቲካ መሪዎች ተቃዋሚ ይሁኑ ስልጣን ላይ ያሉ እራሳቸውን ለሁሉም ዘርፍ ጥያቄ ዝግጁ የሆነ መልስ ያላቸው ይመስላቸዋል። በመሆኑም በኢኮኖሚ በሉት ማህበራዊ ወይም ዲፕሎማሲያዊ ሆነ ወታደራዊ ሁሉን አዋቂ ነን ባዮች ናቸው። በመገናኛ ብዙሀን ላይ ቀርበው ሲናገሩ ወይም በሆነ ጥያቄ ላይ አቋማቸውን ሲፅፉ በተነሳው ጉዳይ ዙርያ ባለ ሙያ እና አማካሪ እንዲያብላላው ዕድል አይሰጡም። ሁሉም ቆራጥ እና ፈጣን መልስ በመስጠት ተገቢ ይሁን አይሁን ፣ መዘዘኛ ይሁን አትራፊ ፣ የበሰለ እና ከመሪ የሚጠበቅ ደረጃ ያለው አመለካከት ይሁን አይሁን ከቶ አያሳስባቸውም።*

*አቶ ዳውድ የ ሻ'ኣቢያ ክብር እንግዳ ናቸው - ኤርትራ 'ቤት ለምቦሳ - እምቦሳ እሰሩ' ብላ ተቀብላቸዋለች። እንደ ቤታቸው ዘና ብለው የሚኖሩባት ፣ የሚወጡ የሚገቡባት አገር ሆናለች። ለዚህ ሁሉ ውለታ አንድ ደብዳቤ ለተመድ መፃፍ የሚበዛ ነገር አይደለም። ይሁንና የሳቸው እና የድርጅታቸው አኳሁዋን አንድ በቅርቡ ከወደ ጀርመን የመጣ ዜና ያስታውሰኛል። ጉዳዩ በአጭሩ ስለ አንዲት ነፃነቷን ያወጀች ላም ነው - እንዲህ ይላል።*

*ኦስትራያ እና ጀርመን ድንበር ባቫርያ አካባቢ ባለፈው ግንቦት ወር ላይ አንዲት ኢቮን የተባለች ላም ከበረት አምልጣ ጥቅጥቅ ያለ ጫካ ውስጥ ተሸሽጋለች። የላሚቱ ባለቤቶች ፈልገው ቢያጧት ጉዳዩን ለፖሊስ ያመለክታሉ። (ፍለጋው እነሆ ይህን መጣጥፍ እስከምከትብበት ሰዓት ቀጥሏል።) ላሚቱ ድንገት ከጫካ ብቅ እያለች አውራ መንገድ ትዘጋለች - ብዙ የትራፊክ መጨናነቅ አድርሳለች። ፖሊስ ተኩሼ ልግደላት ቢልም የእንሰሳ መብት ተሚጋቾች ድርጊቱ በህግ ያስጠይቃል ፣ ኢ-እንሰሳዊ በመሆኑም ይወገዘል በማለታቸው ሊሳካ አልቻለም። ላሚቱን ከነነብሷ በሆነ መንገድ ይዞ ማምጣት ለሚችል ሰው አስር ሺህ ዩሮ ለመክፈል ባለቤቶቿ ይፋ አድርገዋል። ለምሳሌ በፍለጋ ላይ ከተሰማሩት የእንሰሳ ደህንነት ባለ ሙያ አንዱ ሲናገሩ 'ከላሚቱ ጋር አይን ለአይን ተጋጭተናል ፣ አስተያየቷ እንደ ቤት እንሰሳ ሳይሆን እንደ ዱር አውሬ ነው' ብለዋል።*

*የኔን ትኩረት የሳበው እና መደምደሚያዬ ላይ ኢቮን - ላሚቱን ለመጥቀስ የፈለኩበት ግን ለዚች አማፂ ላም ክብር ሲሉ የአካባቢው ሙዚቀኞች የቋጠሩት ስንኝ ነው።*

*'ኢቮን አውሬዋ ላም -*
*የተጎናፀፍሽውን ነፃነት እንዳይነጥቁሽ*
*ጠብቂው ዘላለም!!*

Yvone፣ wild cow
Don’t let them take your freedom

*ኤርትራ ላይ የመሸጉ ብዙ ላሞች እንዳሉ ይሰማኛል - ኤርትራ ግን ለኢትዮጵያ ሆነ ለዜጎችዋ የሚበጅ አንዳች በጎ ነገር ታደርጋለች የሚል ዕምነት ከቶ የለኝም።*

*ኢቮን አሁንም ጫካ ነች - ማታ ማታ ሳር ትግጣለች ፣ ቀን ቀን ሊይዟት ከሚሞክሩ አጥማጆች ጋር ድብብቆሽ ትጫወታለች። ታሪኩን መከታተል ለምትሹ ግርጌ ባስቀመጥኩት መንገድ ማግኘት ይቻላል።*[2]

[2] http://abcnews.go.com/International/activists-save-yvonne-runaway-cow/story?id=14240863